# በወንጀል ህጉና በሌሎች የወንጀል ቅጣት ድንጋጌዎች መካከል ያለው ተዛማጅነት

## አጭር ዳሰሳ

**ጥናቱን ያከናወኑ ባለሙያዎች፡-**

ሰለሞን ወ/ትንሳኤ

አሮን ደጎል

1 አዳዲስ ህጎችን ከማውጣት ይልቅ የወንጀል ህጉን ወጥነት ለመጠበቅ ሲባል የወንጀል ህጉን በማሻሻል

ያልተካተቱ ጥፋቶችን ከነቅጣታቸው እንዲካተቱ ማድረግ፣ ወይም

2 የሚወጡት ህግጋት በተለይ የቅጣት ድንጋጌዎቹ የወንጀል ህጉ አካል ማድረግ ቢቻል

3 ሌሎች ህግጋትን ከማውጣት በፊት በዚህ ረገድ የወንጀል ህጉ ያካተታቸውን ጥፋቶች/የወንጀል ዓይነቶች ከነቅጣት አይነትና መጠናቸው በጥልቀት ቢዳሰሱና አስፈላጊው ጥናት ከተደረገ በኋላ ህግጋቱ ቢወጡ የተሻለ ነው፡፡

4. በጥናቱ ከተዳሰሱት 24 አዋጆች ውስጥ 13ቱ (ከ50 በመቶ/ግማሽ/ በላይ የሚሆኑት ከህገመንግስታዊው የወንጀል ህግ ወደኋላ ተመልሶ አለመስራት መርህ ጋር በግልጽ የሚቃረን ድንጋጌ የያዙ ናቸው፡፡ ይ�ውም ‹‹**በወንጀል ህጉ/በሌላ ህግ የበለጠ የማያስቀጣ ካልሆነ በስተቀር**›› ይህ ድንጋጌ ያለው እንደምታ ተቀጪው የተቀጣበትን ድርጊት ጥፋት አድርጎ በወጣው አዋጅ መሰረት ሊቀጣ ሲገባው በዚያ ጉዳይ ላይ ተደንግጎ የነበረውና በዚህ አዋጅ እንደተሻረ የሚቆጠረው የወንጀል ህጉ የቅጣት ድንጋጌ እንዳጋጣሚ አዋጁ ከሚስቀምጠው ቅጣት በላይ የሚቀጣ ስለሆነ ብቻ እንደገና ወደኋላ ተመልሶ ያንኑ የወንጀል ህግ የቅጣት ተፈጻሚ እንዲሆንበት ይደረጋል፡፡ በዚሁ መርህ መሰረት ግን በመጀመሪያ ደረጃ የወንጀል ህግ ወደኋላ ተመልሶ ተግባራዊ አይሆንም በልዩ ሁኔታ ተግባራዊ ቢሆን እንኳን የበፊቱ ቅጣት ድንጋጌ (በወንጀል ህጉ ውስጥ ያለው) ለተቀጪው የሚጠቅመው/ቅጣትን የሚያቀልለትን ከሆነ ብቻ ነው፡፡ በዚህ በተያዘው አካሄድ ግን ለአንድ ዓይነት የወንጀል ድርጊት ሁለት የተለያዩ የቅጣት አይነቶችን የያዙ እና በአንድ ጊዜ ሁለቱም ተፈጻሚ ሊሆኑ የሚችሉ የተለያዩ ህግጋት ድንጋጌዎችን ነው፡፡ ይህደግሞበወንጀል ፍትህ አስተዳደሩ በተለይም በደኝነት አካሉ ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ ቀላል እንደማይሆን ግልጽ ነው፡፡ ስለዚህም ከዚህ በፊት የወጡትና ከላይ የተጠቀሰውን አገላለጽ የያዙ ህግጋት እንዲከለሱ ወደፊት የሚወጡ ህግጋት ደግሞ በጥንቃቄ እንዲታዩና ከዚህ ዓይነት ችግር ነጻ እንዲሆኑ መደረግ ይኖርበታል::